# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# *Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

**ግንቦት 24 ቀን 2009 ዓ.ም.**

## ኢሕአፓ <u>በጀግናው አርበኛ በኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳ ሕልፈተ ሕይወት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን በቁጭት ይገልፃል !</u>

ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳ መላ ዕድሜያቸውን ያሳለፉት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት፤ ፍትኅ-ርትዕ ፤ ዴሞክራሲ ሥርዓትና ለሀገር ልዋላዊነት ሲታገሉ ነው። በዚኽም ምክንያት የአያሌ ዓመታት እስርና መንገላታት፤ ስደትና ጉስቁልና ተፈራርቀውባቸውል ። ይኽንንም በፀጋ ተቀብለው ፤ በመርኅ ላይ የተመሰረተ ትግል ሲያካሂዱ በመኖራቸው፤ አርአያነተቸው ለዚያ ሰማዕታዊ ትውልድ አንፀባራዊ ኮከብ ሆኖ ቆይቷል ። ወደፊትም በታሪክ እየተጠቀሰ የሚኖር ነው።

ሦስቱን ተፋራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች፤ በግንባር ቀደም ሲታገሉ መኖራቸው፤ የትግል ፅናታቸው እንከን የማየወጣው መሆኑን በተግባር አስመስክረዋል። በተለይ በደርግ ዘመን ኢሕአፓ ነጻ ባወጣው አካባቢ በኢሕአፓ አባልነታቸው ታጋዮችንና አገር ወዳጆችን በማሰባሰብና ለትግል በማነሳሳት ከፍተኛ ጀብዱ ፈጽመዋል። የወያኔ አገዛዝ በሥልጣን ሲሰየምና የአገራችን ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ከፋፋዩንና አምባገነኑን ሥርዓቱ በብርቱ የተቃወሙ ሲሆን ታጋይ ድርጅቶችን በማስተባበር፤ በመምከርና በማበረታት የተጫወቱት ግምባር ቀደም ሚና የሚረሳ አይደለም። በዚኽም እንኮራባቸዋለን። እንወዳቸዋል። እናመሰግናቸዋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ እስከ ፍፃሜ ሕወታቸው ድረስ ከልብ እየወደዱ አልፈዋል ። ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ፍቅራቸውን የገለፁት ፤ ለሥልጣን ጉጉት፤ ለሀብት ክምችትና፤ አላፊ- ጠፊ ለሚሆነው ውዳሴ ከንቱ ሳይሆን በመርኅ ላይ በተመሠረተ ጽኑ ዕምነት ላይ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በዚህ ቀውጢ ዘመኗ፤ ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳን የመሰለ የቁርጥ ቀን ልጅ በማጣቷ ታዝናለች። ሀዘኗ ዕጥፍ ድርብ የሚሆነው ግን፤ ከኢጣሊያ ወረራ አንስቶ፤ እስከአሁኑ የመከራ ዘመኗ ድረስ ፀንቶ ሲታገልላት የኖረው ጀግና ልጇ፤ አስናቀ ዕንግዳ ፤ ለሀገሩ ጥርኝ አፈር ሳይበቃ መቅረቱ ነው። ይከ ደግሞ፤ ቁጭታችንና ብስጭታችን የበለጠ ያጠነከረዋል። ትግላችንን አጠንክረን እንድንቀጥልም ግፊት ይሆነናል ። የአርበኛው ጀግና ክሎኔል አስናቀ እንግዳን ታሪክ የምናከብረው ትግላችንን በመቀጠል እንጅ፤ የሀዘን እንባ በመርጨት አይደለም ። ኮሎኔል አስናቀ፤ መስዋትን እንጅ ፤ ማልቀስን አላስተመሩምና !

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website www.eprp.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ የጀግና ልብና የብርትኡ አዕምሮ ባለፀጋ ስለነበሩ የበርካታ መፃህፍት ደረሲም ነበሩ። ልዩ-ልዩ አረዕስትን ያከተቱ መጽፍትን ለአንባብያን አበርክተዋል ። ጸሃፊም ብቻ ሳይሆኑ የተዋጣላቸው አንባቢም ነበሩ። የዕድሜ ባለፀጋ ሆነው በዚህች ዓለም ጤናማ ሆነው ሕይወት እንዲኖሩ ካደርጓቸው መሠረታዊ ምክንያቶች መካከል፤ በአካል፤ በመንፈስና በአዕምሮ ጤናማ በመሆናቸው ነበር። እነኝህ ባህርያት፤ በህይወታቸው የተፈራረቁባቸውን እንግልትና ችግር በብቃት ለመወጣት አስቸለዋቸዋል ። ተክለ ስብዕናቸውንም ሊመመሠረት የቻለው በዚህ ምክንያት እንደሆነ አንጠራጠርም ።

ኢ. ሕ. ኢፓ. ኮሎኔል አስናቀ ዕንግዳን በክብር ሲሸኝ ፤ ከታላቅ ክብርና ምስጋና ጋር ነው ።፤ ለቤተስባቸውንና ለወዳጆቻቸው መጽናናትን እንመኛለን ።